# የማረጋገጥ ሂደት ተብራርቷል

“ማረጋገጥ” ግምገማ ወይም ምርመራ የሚባልበት ሌላኛው መንገድ ነው። አንድ ሰው ለጥቅማ ጥቅም ብቁ መሆን አለመሆኑን ጥያቄ ውስጥ የሚያስገቡ ጉዳዮች እንዳሉ ስናውቅ፣ ተጨማሪ መረጃዎችን የመጠየቅ እና የመገምገም ሕጋዊ ግዴታ አለብን።

## የማረጋገጥ ሂደት የሚጀምረው መቼ ነው?

ከስራ አጥነት ኢንሹራንስ ፕሮግራም (Unemployment Insurance Program) የሚሰጡ ጥቅማ ጥቅሞችን ለማግኘት ያቀረቡትን ጥያቄ ከላኩልን በኋላ ብቁነትዎን ለመወሰን ጥያቄውን እንገመግማለን። የይገባኛል ጥያቄዎ ውስብስብ ሊሆን ወይም ጥልቅ የሆነ ግምገማ እንድናደርግ የሚጠይቁ ጉዳዮች ሊኖሩት ይችላል። ይህ ደግሞ ማረጋገጥ ተብሎ ይጠራል።

በማረጋገጥ ሂደቱ ወቅት ከእርስዎ እና ከማንኛውም ሌላ ምንጭ አስፈላጊውን መረጃ እንሰበስባለን። ለምሳሌ፣ ጉዳዩ ከቅርብ ጊዜ ሥራዎ ጋር የተያያዘ ከሆነ፣ ብዙውን ጊዜ ከቀድሞው አሠሪዎም መረጃ እንሰበስባለን። ከዚያም የተገኘውን መረጃ እንገመግማለን፣ ለእርስዎ ሁኔታ ያሉትን የስራ አጥነት ኢንሹራንስ ሕጎችና ደንቦች ተግባራዊ እናደርጋለን እንዲሁም ውሳኔ እናስተላልፋለን።

## የይገባኛል ጥያቄዬ እየተገመገመ ያለው ለምንድን ነው?

የስራ አጥነት ኢንሹራንስ ፕሮግራም ሥራቸውን ላጡ ወይም በራሳቸው ጥፋት ባልሆነ ምክንያት የስራ ሰዓታቸው ለተቀነሰ ሰዎች ጥቅማ ጥቅሞችን ይሰጣል። ጥቅማ ጥቅሞችን ለማግኘት ሰዎች ለስራ ዝግጁ መሆን፣ መስራት መቻል እና በየሳምንቱ ሥራን በንቃት መፈለግ አለባቸው። እነዚህን መስፈርቶች ላያሟሉ እንደሚችሉ ካወቅን ጉዳዩን ማጣራትና ለጥቅማ ጥቅም ብቁ መሆንዎን መወሰን አለብን።

ለግምገማ የተለመዱ ምክንያቶችን ዝርዝር በunemployment.oregon.gov/adjudication ላይ ማግኘት ይችላሉ።

# የማረጋገጥ ሂደት ተብራርቷል

State of Oregon Employment Department

## ግምገማው ምን ያህል ጊዜ ይወስዳል?

የይገባኛል ጥያቄዎችን በተቀበልንበት ቅደም ተከተል እንገመግማለን፣ ነገር ግን ውስብስብ የሆኑ ጉዳዮች ለመገምገም ተጨማሪ ጊዜ ሊወስዱ ይችላሉ። ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ሁሉም አካላት ጋር ለመነጋገር፣ እውነታዎችን ለመሰብሰብ፣ ሕጎቹን ለመተግበርና ጥቅማ ጥቅሞችን ለመፍቀድ ወይም ለመከልከል ፍትሐዊ የሆነ ውሳኔ ለማድረግ ጊዜ ያስፈልገናል።

ግምገማችንን በምናደርግበት ጊዜ ጥቅማ ጥቅሞችን መጠበቅ ከባድ ሊሆን እንደሚችል እናውቃለን። ጥልቅ የሆነ ግምገማ ማካሄድ እና ሁሉንም እውነታዎች ማግኘታችን የኦሬጎን ነዋሪዎችን ከማጭበርበር እና ትርፍ ክፍያ መቀበል ከሚያስከትለው ውጥረት ለመጠበቅ ይረዳናል። ትርፍ ክፍያ መቀበል እርስዎ ብቁ ባልሆኑበት ጊዜ ጥቅማ ጥቅሞችን ሲቀበሉ እና ገንዘቡን መልሰው መክፈል ሲኖርብዎት ነው።

## እንዴት ነው የምታገኙኝ?

የይገባኛል ጥያቄዎ ማረጋገጥ የሚጠይቅ ከሆነ አንድ አረጋጋጭ – የይገባኛል ጥያቄዎን የሚያጣራ ሰው – በስልክ፣ በፖስታ እና በኢሜይል ያነጋግርዎታል። የጽሑፍ መልእክት አንልክልዎትም። ስልክ ካለዎት እባክዎን፣ ላልታወቁ ቁጥሮችም ቢሆን፣ ስልኩን ይመልሱ፣ እንዲሁም የድምጽ መልዕክት መቀበያዎ ከኦሪጎን የቅጥር መምሪያ (Oregon Employment Department) የሚደውል ሰው የድምጽ መልዕክት መተው እንዲችል የተዋቀረ መሆኑን ያረጋግጡ።

እባክዎን ከኦሪጎን የቅጥር መምሪያ (Oregon Employment Department) ለሚመጡ ደብዳቤዎች እና የድምፅ መልዕክቶች ሁሉ መልስ ይስጡ። አንድ ግንኙነት ከእኛ የተላከ ስለመሆኑ እርግጠኛ ካልሆኑ ወይም አንዳንድ ግንኙነቶች የማጭበርበር ሊሆኑ ይችላሉ የሚል ስጋት ካለዎት፣ እባክዎን ለእርዳታ ያነጋግሩን።

አድራሻዎን በFrances Online በ frances.oregon.gov ማዘመንዎን ያረጋግጡ።

# የማረጋገጥ ሂደት ተብራርቷል

## አሁን ምን ማድረግ ይኖርብኛል፣ እንዲሁም ግምገማውን እንዴት ማፋጠን እችላለሁ?

1. ለሳምንታትዎ ክሬዲት ማግኘት እንዲችሉ በግምገማው ወቅት ሳምንታዊ የይገባኛል ጥያቄዎችን ማቅረብዎን ይቀጥሉ። ለጥቅማ ጥቅሞች ብቁ እንደሆኑ ከወሰንን ሊከፈልዎት የሚችለው በጊዜው ለጠየቋቸው ሳምንታት ብቻ ነው። በኋላ ላይ ተመልሰው ሊጠይቁ አይችሉም።
2. እባክዎ ለምንልክልዎት ደብዳቤ ሁሉ መልስ ይስጡ። ደብዳቤውን በፖስታ መላክ ወይም "እኛን ያነጋግሩን" የሚለውን ቅጽ መጠቀም ይችላሉ። የምንጠይቀው መረጃ ይለያያል። ለምሳሌ፣ የሚከተሉትን እንዲያደርጉ ልንጠይቅዎ እንችላለን፦
    - የአሰሪዎን መረጃ ግልጽ ያድርጉ
    - ሳምንታዊ የሥራ ፍለጋዎችዎን ሪፖርት ያድርጉ
    - ከሥራ ለምን እንደለቀቁ፣ ከሥራ ለምን እንደተባረሩ ወይም ጥቅማ ጥቅሞችን በሚጠይቁበት ጊዜ አዲስ ሥራ ለመቀጠር ፈቃደኛ ያልሆኑበትን ምክንያት ይግለጹ
    - ጥቅማ ጥቅሞችን በሚጠይቁበት ጊዜ ለሥራ የማይገኙ ወይም መሥራት የማይችሉ ከነበረ መረጃ ይስጡ
    - የመገኛ መረጃዎን ያዘምኑ
3. ስልክ ካለዎት፣ የድምጽ መልዕክት መቀበያዎ ከኦሪጎን የቅጥር መምሪያ (Oregon Employment Department) የሚደውል ሰው የድምጽ መልዕክት መተው እንዲችል የተዋቀረ መሆኑን ያረጋግጡ።
4. እባክዎን ከኦሪጎን የቅጥር መምሪያ (Oregon Employment Department) ለሚመጡ ደብዳቤዎች እና የድምፅ መልዕክቶች ሁሉ መልስ ይስጡ። አንድ ግንኙነት ከእኛ የተላከ ስለመሆኑ እርግጠኛ ካልሆኑ ወይም አንዳንድ ግንኙነቶች የማጭበርበር ሊሆኑ ይችላሉ የሚል ስጋት ካለዎት፣ እባክዎን ለእርዳታ ያነጋግሩን። መረጃን ለእኛ ለመላክ ቀላሉ እና ፈጣኑ መንገድ በunemployment.oregon.gov/contact ላይ ባለው "እኛን ያነጋግሩን" በሚለው ቅጽ በኩል ነው።

## በውሳኔው ካልተስማማሁስ?

በግምገማችን ማብቂያ ላይ ለጥቅማ ጥቅም ብቁ መሆንዎን ወይም አለመሆንዎን እንወስናለን። ያም ሆነ ይህ ውሳኔ እንልክልዎታለን። በውሳኔው ካልተስማሙ ይግባኝ የመጠየቅ እና በአስተዳደራዊ ህግ ዳኛ ፊት ችሎት የመጠየቅ መብት አለዎት። በተጨማሪም አሰሪዎ ለይገባኛል ጥያቄዎ በወሰነው ውሳኔ ላይ ይግባኝ የመጠየቅ መብት አለው። ይግባኝ ለማለት ከወሰኑ፣ የችሎቱን ውጤት በሚጠብቁበት ጊዜ ጥቅማ ጥቅሞችን መጠየቅዎን ይቀጥሉ።

ውሳኔውን እንልክልዎታለን፤ እንዲሁም እንዴት ይግባኝ መጠየቅ እንደሚቻል መመሪያ ይኖረዋል። ተጨማሪ መረጃ በunemployment.oregon.gov/appeals ላይ ማግኘት ይችላሉ።

# የማረጋገጥ ሂደት ተብራርቷል

## አሁን እርዳታ ቢያስፈልገኝስ?

የማረጋገጥ ሂደት ጊዜ የሚወስድ ሲሆን አሁን እርዳታ ሊያስፈልግዎት እንደሚችል እንገነዘባለን። እንደ የጤና ሽፋን እና በማህበረሰብዎ ውስጥ ወደሚገኙ ሌሎች እርዳታዎች የሚመሩ አገናኞች ያሉ አንዳንድ የመረጃ ምንጮች እዚህ ቀርበዋል።

### WorkSource Oregon

የWorkSource Oregon ቢሮዎች ሰራተኞችን ጥሩ ሙያን ለመገንባት ከሚያስችሉ የመርጃ ሃብቶች ጋር ያገናኛሉ። ሰዎች ትምህርቶችን መውሰድ፣ የልምድ ማስረጃ ለመፃፍ ዕገዛ ማግኘት፣ የሥራ ማጣቀሻዎችን ማግኘት እና ሌሎችንም በመላ ስቴቱ በሚገኙ ቦታዎች – ወይም በመስመር ላይ ማግኘት ይችላሉ!

ስለአገልግሎቶች እና ቦታዎች መረጃ በworksourceoregon.org ላይ ይገኛል።

### የጤና ሽፋን

የጤና ሽፋንዎን ካጡ ወይም የጤና ሽፋን ከሌለዎት ነፃ ወይም አነስተኛ ዋጋ ያለው የጤና ሽፋን ለማግኘት ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ። healthcare.oregon.gov ን ይጎብኙ ወይም ወደ 1-855-268-3767 ይደውሉ።

### 211info

211info በኦሪገን ውስጥ ወይም በአካባቢዎ ማህበረሰብ ውስጥ የሚገኙ እንደ የቤት ኪራይ ክፍያና የፍጆታ ክፍያዎችን ለመክፈል፣ እና ሌሎች ጥቅማ ጥቅሞችን ለማግኘት የሚረዱ ሌሎች መርጃ ሃብቶችን ለማግኘት ሊረዳዎ ይችላል።

ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት እና መርጃ ሃብቶች የሚገኙበትን ለማወቅ 211info.orgን ይጎብኙ።

በተጨማሪም የሚከተሉትን ማድረግ ይችላሉ:- ወደ 2-1-1 ወይም 1-866-698-6155 ይደውሉ

(ነፃ የቋንቋ አስተርጓሚዎች ይገኛሉ) ለTTY 711 ይደውሉ እና ወደ 1-866-698-6155 ይደውሉ

ዚፕ ኮድዎን በጽሑፍ ወደ 898211 (TXT211) ይላኩ (በእንግሊዝኛ እና በስፓኒሽ)

ኢሜይል ወደ help@211info.org (በእንግሊዝኛ እና በስፓኒሽ) ይላኩ